# ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መርሆችን በማሕበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች ውስጥ ማካተት

## ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መሳሪያ ምንድን ነው?

የመንግስት በጀት አዋቂ ሴቶችና ወንዶች፤ በሴትና ወንድ ልጆች ህይወት ላይ የተለያየ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት *(ጀንደር ሪስፖንሲቭ በጀቲንግ)* የመንግስት በጀት በሴቶችና በወንዶች መካከል እኩልነት እንዲሰፍን አስተዋጽኦ ማድረግና አለማድረጉን የሚገመገምበትና የሥርአተ-ጾታ እኩልነትን የሚያያበረታቱ ለውጦች የሚተዋወቁበት ሂደት ነው፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከተባበሩት መንግስታት የሴቶች ዘርፍ፤ ፓኔ *(ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲፊል ሶሳይቲስ ኢን ኢትዮጲያ)* የተባለ ጥምረት፤ ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅትን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሙከራ አካሂደውታል፡፡ ኢሳፕ2 ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅትን በማሕበራዊ ተጠያቂነት መምሪያ ውስጥ በማካተት መሳሪያውን በአገር አቀፍ ደረጃ ያሰራጨ ቀዳሚ ፕሮግራም ነው፡፡ ኢሳፕ2 ለአጠቃቀም አመቺ የሆነ ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መምሪያ አዘጋጅቶ ማሕበረሰቡ እንዲጠቀምበት አድርጓል፡፡ ይህ መሳሪያ በተሳትፎና፣ በተግባር እየተፈተሸ ተሻሽሎ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅትን በሌሎች የማሕበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች ውስጥ ለማካተት ያግዛል፡፡

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች እኩል ተደራሽ እንዲሆኑ፤ እኩልነትን ለማስፋፋት፤ እንዲሁም ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ለፍላጎቶቻቸው ምላሽ እንዲያገኙ ያግዛል፡፡ እንዴት? "ይህ የእቅድ ወይም የበጀት አካል አዋቂ ሴቶችና፣ ታዳጊ ሴቶች፤ አዋቂ ወንዶችና ታዳጊ ወንዶች ላይ ምን ተጽዕኖ ያመጣል" የሚለው ጥያቄ መጠየቁን በማስረገጥ ሁሉም የእቅድና የበጀት ዝግጅት ደረጃዎች ከሥርዐተ ጾታ አንጻር እንዲጤኑ በማድረግ ነው፡፡

ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መምሪያ - ስድስቱ ደረጃዎች

- **ደረጃ 1**፡- የሥርዐት ጾታና የበጀት ባለሙያዎችን፤ ከተመረጠው ዘርፍ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ተጠሪዎችን መለየት - ይህ አብዛኛውን ጊዜ አቅምን ማደራጀት (*ሪሶርስ ማፒንግ*) ይባላል፡፡ ተለይተው የታወቁትን ሰዎች በማሕበራዊ ተጠያቂነት ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ መጋበዝ፡፡ በተግባር እንደታየው ይህ ሂደት ብዙ ጊዜ የወረዳው ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት፤ የፋይናንስ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት፤ እንዲሁም ከግብርና፣ ከውሀና የአካባቢ ንጽሕና፣ ከጤና፣ ከትምህርትና ከገጠር መንገዶች ጽ/ቤት ተጠሪዎችን ወይም የሚመለከታቸውን ሰራተኞች ያካትታል፡፡
- **ደረጃ 2፡- ከበጀት ዑደቱ አንጻር መቃኘት** – የማሕበራዊ ተጠያቂነት ሂደቶችን ዜጎች በጀትን አስመልክቶ የሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር በሚያስችላቸው መልኩ ማቀድ፡፡
- **ደረጃ 3፡- በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሥርዐተ ጾታ ፍትህዊነትን በተመለከተ ሥልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች፡-** ከላይ በደረጃ 1 ለተለዩት ባለሙያዎች ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት ላይ ሥልጠና መስጠትና እነዚህ ባለሙያዎችና ከአገልግሎት ተቀባዩ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ አገልግሎት ሰጪዎች የሥርዐተ ጾታ ፖሊሲዎችን ለዜጎች እንዲያብራሩ አብሮ መስራት፡፡
- **ደረጃ 4፡- የሥርዐተ ጾታ ትንተና፡-** አዋቂ ሴቶችን፣ ታዳጊ ሴቶችን፣ አዋቂ ወንዶችንና ታዳጊ ወንዶችን የማሕበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች በሚተገበሩበት ሂደት ውስጥ ማሳተፍ፡፡ የሥርዐተ-ጾታ ትንተናን የአገልግሎት አሰጣጡ ግምገማ አካል ማድረግ፡፡ በደረጃ 1 ከተለዩት መካከል የሥርዐተ ጾታ ቅርበት ያለው ባለሙያ ይህን ሂደት ሊመራው ይችላል፡፡
- **ደረጃ 5፡- የፊት ለፊት ውይይቶች/የበጀት ውይይት መድረኮች፡-** በፊት ለፊት ውይይቶችና በበጀት ውይይት መድረኮች፡- በበጀት ፎረም አጀንዳዎች ውስጥ የሥርዐተ ጾታ ጉዳዮች በመወያያ ርዕሶች ዝርዝር ውስጥ ማስገባት፡፡ የማሕበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮችና የማሕበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴዎች በሴቶችና ለችግር ተጋላጭ በሆኑ ወገኖች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የቀረቡ ችግሮች በጋራ የድርጊት መርሀ-ግብሩም ላይ በተገቢው መልኩ ቅድሚያ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
- **ደረጃ 6፡- በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለሴቶችና ለወንዶች የተደረጉ መሻሻሎችን መገምገም** – በፊት ለፊት ውይይት/በበጀት ውይይት መድረኮች ወቅት ስምምነት ላይ በተደረሰው መሰረት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የተደረጉ መሻሻሎች በእርግጥም ሴቶችንና ወንዶችን አየጠቀሙ መሆናቸውን መከታተል፡፡

## *ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ለታዩ መሻሻሎች አስተዋጽኦ አድርጓል*

ጥቂት በማይባሉ ሥፍራዎች ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መርሆዎች በማሕበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች ውስጥ መካተታቸው በአገልግሎት አሰጣጡ አድሎ የሚታይባቸው አንዳንድ ድርጊቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲቀረፉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት በምሳሌ የሚጠቀሱ ውጤቶች ናቸው፡፡

**ጤና**

- በጤና ጣቢያዎች ተጨማሪ አልጋዎች
- ተጠቃሚን የሚያቀርብ የአገልግሎት አሰጣጥ
- አገልግሎት መስጫዎች ለተጨማሪ ሰዐታት ክፍት መሆን
- ወደ አገልግሎት መስጫ የሚያደርሱ የተሻሉ መንገዶች
- የማዋለጃና የመጠበቂያ ክፍሎች መስፋፋት
- አምቡላንሶች እናቶችን ከወሊድ በኋላ ወደየቤታቸው እንዲያደርሷቸው ስምምነት ላይ መድረስ

**ትምህርት**

- የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢን ደህንነት ለመጠበቅ አጥር ማጠር
- መጸዳጃ ቤቶችን ለሴትና ወንድ ተማሪዎች መለየት
- ሴት ልጆች ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ማበረታታት
- ትምህርት እንዳያቋርጡ መከላከል
- ሴት ልጆች እኩል የትምህርት እድል እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ውሀ መቅዳት፣ ህጻናት መንከባከብ፣ የቤት ውስጥ ሥራዎችን የመሳሰሉ ጾታ-ተኮር የሥራ ክፍፍሎች ላይ ሕብረተሰቡ ተወያይቶባቸዋል፡፡

**ግብርና**

- ሴቶችን በጓሮ አትክልት፣ በዶሮ እርባታና በወተትና ወተት ተዋጽኦዎች ማሰልጠን
- መስኖን ጨምሮ ሴቶችን በተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ማሰልጠን

**ውሀና የአካባቢ ንጽሕና**

ወደ መኖሪያ ቤት የቀረቡ ተጨማሪ ውሃ መቅጃዎች፡-

- ሴት ልጆች ውሀ ለመቅዳት የሚወስድባቸውን ጊዜ አሳጥሮላቸዋል
- ሴት ልጆች ላይ ያለውን የሥራ ጫና አቅልሎላቸዋል
- የሴቶችን የትምህርት ቤት ምዝገባ መጠን ከፍ እንዲል ሲያደርግ የጥናት ሰዓት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡

**ገጠር መንገድ**

- ሴቶች ልጆች በትምህርት ቤት መንገድ ላይ፤ በውሀ መቅጃ መንገድና እንጨት ለቀማ ሲሄዱ የሚደርስባቸው ጥቃት በመላው ማሕበረሰብ ትኩረት የተሰጠበት ጉዳይ ሰሆን ችግሩን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶችም ተቀምጠውለታል፡፡
- ሴቶች ነዋሪዎች ችግሮችን በለዩበት ወቅት በአካባቢው ለመዘርጋት የታቀዱ አዳዲስ መንገዶች ወደ ገበያና ጤና ጣቢያ የሚያደረሱና ቀና በሚሆኑበት አግባብ ቅየሳቸው እንዲለወጥ አድርገዋል፡፡

## *ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መርሆዎች በማሕበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች ውስጥ በመካተታቸው የታዩ ግኝቶች*

- ኢሳፐ2 ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት መርሆዎች በማሕበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች ውስጥ ማካተት መቻሉን አረጋግጧል
- ወደፊት ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት ሲተገበር የምክር ቤት አባላትን በማሳተፍ የሥርዐት ጾታ ችግሮችን አጉልቶ ማሳየትና ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ የመንግስትን ተጠያቂነት ማጠንከርና ችግሮቹም ቸል እንዳይባሉ ማድረግ ይቻላል፡፡
- ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅት ላይ የሚሳተፉ ቁልፍ አካላት፡- የመንግስት ዕቅድ ባለሙያዎች፣ የበጀት ሰራተኞች፣ የክትትልና ግምገማ ባለሙያዎች፣ ለጋሽ ድርጅቶችና የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች አቅማቸውን ተቋማዊ መልክ ለማስያዝ ስልታዊ ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡
- ለሥርዐተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የበጀት ዝግጅትን ልምዶች መቀመርና ከሌሎች ጋር መጋራት መሳሪያውን በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲለመድ ያስችላል፡፡